# ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም

ተኮላ መኮንን

tekolamekonen@yahoo.com

ባለፈው በታዘብኩት ትዝብት ላይ ባቀረብኩት አስተያየት ምክንያት “ቅጥረኛ ወታደር” በሚል ለተጻፈ ምላሽ ማቅረቤ ይታወሳል። በወቅቱ እንደኔው ጉዳዩ ያሳሰባቸው ግለሰቦች አስተያየት ሲሰነዝሩ እንደነበርም አስታውሳለሁ። ነገሩ እየተፋፋመ ሲሄድ እየጎነታተሉኝም ዝም ማለት መርጬ ነበር። አሁን ሁኔታው ተቀይሮ በብእር ሥም የሚጽፉትን ግለሰብ “አንተ ካባህን አውልቅ እናውቅሃለን” በሚል የግለሰብ ሥም እየተጠቀሰ መወራረፍ ተጀመረ። መልእክቱ ሳይሆን መልእክተኛው መጥፎ ነውና መልእክተኛውን መስደብም ጀግንነት ተባለ መሰለኝ ውርጅብኙ ቀጠለ። እስካሁን በምልልሱ የተማርነው ነገር ማ ጥሩ ይሳደባል የሚል ብቻ ሆነ። በነገራችን ላይ ሥማቸው ባደባባይ የወጣውን ከሚጽፉት የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ መምህር የሆኑትን ግለሰብ በአካል አላውቃቸውም። ነገር ግን አዲስ አበባ ተቀምጠው ለሚሰነዝሩት ልበ ሙሉነት ያዘለ መልሳቸው ግን አክብሮቴን ሰጥኋቸው። አንድ ግለሰብ በብእር ሥም የሚጽፈው አንድም በሚጽፈው አደጋ እንዳይደርስበት፣ ካልሆነ በሥሙ ቢጽፍ ከጽሑፉ ይልቅ ሥሙ ክብደቱን እንዳይሸፍነው፣ ወይንም እንዳያቃልለው፣ ካልሆነም የሚጽፈውና እሱነቱ ስለማይጣጣሙ ይመስለኛል። ታዲያ ይህንን እንደ መርህ ከወሰድን ትኩረት መደረግ ያለበት መልእክቱ ላይ ቢሆን ሁላችንም ለግንዛቤ የሚያበቃ ሃሳብ መቃረም እንችል ነበር ብዬ አምናለሁ።

ይህንን እንደ መግቢያ ካልኩ በኋላ ወደ ተነሳሁበት ፍሬ ነገር ላምራ። በነገራችን ላይ በኢሜል ላበረታታችሁኝ በኢሜል ለሰደባችሁኝ ሁሉ ምስጋና እያቀረብኩ ምስጋናዬ ባታነቡት ኖሮ አታመሰግኑኝም አትሰድቡኝም ነበር ከሚል መሆኑን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ።

ባሁኑ ወቅት ሁላችንም መዋጋት ቀርቶ በሰላማዊ መንገድ በውይይት ስህተቶችን በመጠቋቆም፣ ችግሮችን በማቅረብ፣ ለመፍታት እንሞክር፣ የጠመንጃ አብዮት ያብቃ፣ እያልን ነው። ይህንን ካልተቀበልን በጠመንጃ ብቻ የምንፈራረጅ ከሆነ ለማካካስ ሲባል መጨራረስ ሊመጣ ነው። ይህንን የጠመንጃ ትግል ደግሞ በምንም መልኩ መቃወም ኃላፊነት የሚቀበል ግለሰብም ሆነ ቡድን አቋም መሆን ይገባዋል። ትላንትና የአንድ ብሔር የበላይነት ትክክል አይደለም ያልን ግለሰቦችና ቡድኖች፣ ዛሬ በምንም መልኩ ቃላችንን ሳናጥፍ ያንኑ መፈክር መድገም መቻል አለብን። ካልሆነ ሌላው ሲያደርገው ስህተት እኛ ስናደርገው እውነት ያስብላል። መማር ማለት ነገሮችንን አመዛዝኖ በአንድ ነገር ላይ የዳበረ እውቀት መኖር መሆን አለበት እንጂ ሌላውን ማጥላላትና ጥላሸት መቀባት ከሆነ አላዋቂነት ያሰኛል።የሰዎስተኛ ክፍል ተማሪ የኮሌጅ አስተማሪ ለመሆን ከበቃ ማወደስ

እንጂ ማጥላላትን ምን አመጣው? "ገብርኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ ሆኖ ሚካኤልን የሚሳደብ ቅን ክርስቲያን እንዳልሆነ ሁሉ የሁሉንም የተለየ ሃሳብ በጅምላ እየዳመጡ የአካባቢን ድጋፍና ጭብጨባ ለማግኘት መጣር አላማ አልባና አዙሮ አለማየት ድክመት እንጂ ጥንካሬ አይሆንም። የትግራይ ሕዝብ ባለፈው እንዳልኩት ለዘመናት ለኢትዮጵያ አንድነት የተፋለመ፣ በእምነቱ የሚኮራ፣ በታሪኩ የማይሸማቀቅ ኩሩ ሕዝብ ነው። የዛኑ ያክል የአማራውም ሕዝብ ለኢትዮጵያዊነቱ ደምን የከፈለ፣ ለሃገር አንድነት የተዋደቀ፣ ለሃይማኖቱ ቀናዊ የሆነ የሚያኮራ ታሪክ ያለው ሕዝብ ነው። የዓለም ታሪክ ደግሞ ብልጽግናውም ጭምር በጦርነት ዙሪያ ያጠነጠነ ነውና በሃገራችንም የተከሰቱት ከዚህ ውጪ ሊሆን እንደማይችል መስማማት ሲቻል የድሮውን ቁርሾ ችግር በገጠመ ሰዓት ሁሉ መደጋገሙና ማንሳቱ ማብቃት ይኖርበታል። ለነበሩት ችግሮች ደግሞ የአማራው የገዢ መደብ እንደሚወቀሰው ሁሉ የትግራይ የገዥ መደብ ከሃላፊነት ነጻ እንደማይሆን መቀበል አዋቂነት ነው እላለሁ። ቀደም ባለው ጽሑፌ እንደጠቀስኩት ሁሉ ሃገራችን የብሔሮች እስር ቤት ነበረች ብለን በጋራ መጮሃችን እውን ሆኖ እያለ ከ 25 ዓመት በኋላ ያንኑ ቅኝት የምንቃኝ ከሆነ ችግሩ ከመንግሥት ጫንቃ አይወርድም።

ባንድ ወቅት የተባለ ቀልድ ላጫውታችሁ። አንድ አካባቢ የሚኖሩ ጎረቤታሞች በድንበር ተጣሉና ፍርድ ቤት ሄዱ ይባላል። ከፍርድ ቤት ቀጠሮ በፊት ከሳሽና ተከሳሽ ቤተክርስቲያን ሄደው መጸለይ ይጀምራሉ። አንደኛው "ጌታ ሆይ ይህንን ባላንጣዬን ዶግ አመድ አድርግልኝ" ብሎ ይለምናል። ተቀናቃኙ በበኩሉ እዚያው ቤተክርስቲያን ውስጥ ፈንጠር ብሎ "እባክህ ይህንን ባላንጣዬን ከምድረ ገጽ አጥፋልኝ" እያለ ይማጸናል። በዚህ መካከል ለፈጣሪ የሚሳነው ነገር የለምና በአካል ይገለጣል። ቤተክርስቲያኑም በብርሃን ይሞላል። እንዳጋጣሚ እዚሁ ቤተክርስቲያን ጥግ ይዞ የሚጸልይ የነኝህ ተፎካካሪዎች ጎረቤት የሆነ ግለሰብ እየጮሁ የሚለምኑትን ግለሰቦች እያዳመጠ ቆሞ እያለ ፈጣሪ ወደ እሱ ፊቱን በመመለስ "የእነሱንስ ሰምቻለሁ ላንተ ደግሞ ምን ላድርግልህ?" ብሎ ቢጠይቀው ግለሰቡ "ጌታ ሆይ እኔ ምንም አላስቸግርህም እንደሰማኸው የእነሱን ጸሎት ብቻ ስማቸው" አለ ተብሎ ይቀለዳል። ማለት የፈለግሁት ችግራችንን እራሳችን እንፍታ እንጂ ለሌላ አሳልፈን ለመስጠት አንሞክር ነው።

ወንድሞቼ በስድብ የሚሸማቀቅ በራሱ እምነት የሌለው ብቻ ነው። ብናስበው እኮ ለመዋጋት ጊዜው እንዳበቃ ሁሉ ለመሰዳደብም አርጅተናል። ሃሳብ የሰነዘረን ሁሉ ለማሸማቀቅ መነሳት ደግሞ የሃሳብ እጥረት መኖርን፣ አለመብሰልን፣ ተከትሎ የሚመጣን ሃሳብ በመፍራት ወይንም እንደ ፈረንጆቹ አባባል "ጥሩ መከላከያ ነገር አስቀድሞ ጥቃት መሰንዘር ነው" የሚሉትን በመከተል የመጣ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው።

ዛሬ ከተደማመጥን ላነሳቸው የምፈልጋቸው ነጥቦች አሉኝ።

የትግራይ ተወላጅ መሆን ማለት TPLF መሆን ማለት እንዴት ይሆናል ?

TPLF ደግሞ የማይነቀፍ፣ የማይደፈር ጽላተ ሙሴ ነው ካላልን በስተቀር ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች የታያቸውን የድርጅቱን ስህተት ቢጠቁሙ እንዴት ጸረ ትግራይ ሕዝብ ናቸው ተብሎ በደጋፊዎች ይወነጀላሉ።

የ EPRDF ን ፖሊሲ መተቸት ጸረ ኢትዮጵያ እንዴት ያስብላል ? ይህንን ማለት ሂስን መሸሽ አይደለምን ?

ስለ ቅማንት መብት እያወሩን ቆይተው ስለወልቃይት መነገር ሲጀመር አካኪ ዘራፍ ማለት ምን ማለት ነው ? እኛ በናንተ ጉዳይ ያገባናል እናንተ ግን አያገባችሁም ማለት አይደለምን ?

በሕገመንግስቱ መሰረት ክልሎች የራሳቸውን ከባቢ የማስተዳደር ሙሉ መብት ተሰጥቷቸዋል ተብሎ ተደንግጎ ይህም በተግባር እየተካሄደ እያለ የክልሉ ሕዝብ ሳይሆን የሌላ ክልል ግለሰቦች መሪዎቻችሁን ካላወረዳችሁ ብለው ሲነሱ በሕግ አምላክ ማለት ለምን ያሰድባል ?

ሻሸመኔ ኤርትራውያን ነበሩ ጃማይካዎችም ይኖራሉ ማለትና ሻሸመኔ የኤርትራ ከተማ ነች፣ የጃማይካ ምድርነች አንድ ነወይ ? የህንንስ ብሎ አንዱ ቢነሳ ሁላችንስ ዝም እንላለን ወይ ?

እነዚህ የትግራይ ተቆርቋሪ ነን ባይ ለሆኑ ግለሰቦች ልጠይቃቸው የምወደው ነገር ቢኖር የትግራይን ትልቅነት ስንቀበል በሌላ ጎን አማራ "ጽአዳ አፍንጫ" ነው ብለን የተቀበልን ይመስላቸው ይሆን ? ከመሰላቸው ተሳስተዋል።

TPLF እና EPRDF ድርጅቶች ናቸው እንጂ ሃገር ሕዝብ አይደሉም። ከሕዝብ አካል የወጡ አታጋይ ድርጅት መሆናቸውን እንቀበል። እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ለሚሰሩት ምስጋናን ለሚያጠፉት ወቀሳን ለመቀበል ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ይህንን የማነሳው ነገሮችን በስፋት ካላየናቸው የሚነሱትን ሁሉ በማፈን ሰላም ይፈጠራል ብዬ ስለማላስብ ነው።

ኢሕአደግም ሆነ መንግሥት የመልካም አስተዳደር ችግር እንዳለ ተቀብለናል ሲሉ ሕዝቡ ያነሳቸው አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎች አሉ ማለታቸው መሆኑ ይገባኛል። እዚህ ላይ ከተስማማን ለተነሱት ጥያቄዎች መንግሥት መልስ እየሰጠሁ ነው ካለ የመልሱን ውጤት እንደመጠበቅ ነገሮችን በማክረር የሚገኝ ነገር ለእኔ አልገባህ ብሎኛል።

ችግር የለም ብለን ለመደፋፈን እንሞክር ትናንሽ በግሌ የገጠመኝን ላንሳ።

የኤርትራውያን ንብረት መመለስ ላይ ምንም ቅሬታ ሳይኖረኝ ኤርትራውያን የሆኑትን ለመለየት በሚል በተፈጠረ ችግር ግን መሃል ሜዳ የተወለደ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ለመወለድህ ማስረጃ አቅርብ ሲባል ሚዛኑ የደፋ መሰለኝ። የሚገርመው በቦሌ የወጣ ፓስፖርት ያለው ግለሰብ የተቃጠለ ፓስፖርቱን አቅርቦ እንደማስረጃ ሲወሰድለት በወልቃይት በኩል የወጣ ስደተኛ ኢትዮጵያ መወለዱን ማረጋገጫ ምን ይዞ ይቅረብ ? በስደተኛውም መካከል ልዩ ነት እየተፈጠረ አይደለም ወይ ? በሱዳን በኩል ካለፈው ታጋይ ስደተኛ ይልቅ በቦሌ የወጣ የኢሰፓ አባል ክብር ኖሮት ማየት ካላናደደ ምን ያናድዳል ?

ቀደም ባለው ጽሑፌ እንዳልኩት ማንም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም ክልል የመንቀሳቀስ የመስራት መብቱን እየተቀበልኩ ማንም መባረሩን መፈናቀሉን ትክክል አለመሆኑን እየተቀበልኩ ይህን ለማጠናከር የሚጻፉ ጽሑፎች ግን እየገረሙኝ ነው። በተደጋጋሚ ሲባል የሰማሁት ነገር እኛ እኮ ከትግራይ አማራ አላባረርንም የሚል ሆኖ አገኘሁት። ለመሆኑ ይህንን እንደ መከላከያ ካመጡት አይቀር ምን አማራ ነበረና ነው አላባረርንም የሚባለው ? በድልድል የተመደበውን ተማሪ ለማለት ነው ወይስ በጣልያን ውጊያ ጊዜ ዘምቶ እዛው የቀረውን ሕዝብ ማለታቸው ይሆን ? ካልሆነስ ሰውን ማባረር ትክክል አይደለም እንበል እንጂ አላባረርንምን ምን አመጣው ?

ትግርይን ያስተዳድሩ የነበሩት ልዑል መንገሻ ስዩም ተጠንቅቀው የመለሱትን የ VOA ቃለ ምልልስ ሳዳምጥ ያከበርኳቸው “እኔ እስከማውቀው ድንበራችን ተከዜ መለስ ነበር አሁን ግን ያለው የፖለቲካ ውሳኔ ነውና እዛ ውስጥ አልገባም” ሲሉ ሳዳምጥ ነው። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት የአማራውና የትግራይ ልኡላን እንደነበሩም ብልጭ አለብኝ።

ከሁሉም እየገረመኝ ያለው ሌላው ጉዳይ ደግሞ የሃሳብ ልዩነት አለኝ የሚል ግለሰብ ለትግሎ ያበረከተው አስተዋጽኦ ይረሳና የነበረው የፖለቲካ አመለካከቱ ይቀበርና “ትምክህተኛ” ተብሎ “የድሮውን ስርዓት ለመመለስ የሚጥር” ተብሎ ሲወነጀል አስተውላለሁ። የድሮውን ስርአትማ ታግሎ ጣለ። ታግሎ የጣለውን እንዴት አድርጎ ይመልሰዋል ? ደግሞ እኮ ያ የፊውዳል ስርአት ከተገረሰሰ እኮ አርባ ዓመት በላይ ሆነው። ኦሮሞ ሆኖ በደል ደረሰብኝ የሚልን ግለሰብም ሆነ ቡድን ችግሩን አዳምጦ መፍትሄ እንደመፈለግ “ጠባብ” ብሎ መወንጀል መፍትሄ እንዴት ያመጣል ተብሎ ይታሰባል ? አማራውን ትምክህተኛ፣ ኦሮሞው ጠባብ ያ

ብሔር የተቃዋሚ ደጋፊ፣ ይኸ ደግሞ የትምክህተኞች ቀፍቃፊ እየተባለ መቀጠል መፍትሄ ይሆናል ማለት ስህተት አይደለም ወይ? ከዚህ የባሰ ምን ትምክህት አለ? ያነሳሁት ከልብ ስለሚገርመኝ ነው።

ሌላው ነጥብ ላነሳ የምፈልገው ለምንም ጽሑፍ ማጣፈጫ ሆኖ የማነበው ኢሕአፓ ኢሕአፓ የሚለው ነገር ነው። እኔ በምኖርበት አካባቢ እንዲሁ ውይይት ስናካሂድ አንስቼው የነበረውን ዛሬም ላንሳው። ኢሕአፓ ቀንቶት ስልጣን ላይ ወጥቶ ቢሆን ኖሮ እኮ ስልጣን የሚጨብጡት የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ግለሰቦች ነበሩ ብዬ ነበር። አንዱ ቀጠል አደረገና አዎ እውነት ነው ያውም የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች አለ። እነማን ነበሩ የኢሕአፓ መሪዎች፡

ተስፋዬ ደበሳይ

ብርሃነ መስቀል እረዳ

ዘርዐ ክሕሸን

ፀሎተ ዮሐንስ

ዳዊት ስዩም ልቀጥል እንዴ። ይህ ምን ፋይዳ ይፈጥራል። የግራ ፖለቲካ ተከታይ ኢትዮጵያዊ ሆነው የታገሉ ስለነበረ በጠባብነት ተወንጅለው አያውቁም። እንዴውም “አባይ ኢትዬጵያ” ተብለው ተሰደበው ነበር። ስድብ ከተባለ ማለቴ ነው። ኢሕአፓ ሆኖ መታገል ወንጀል አልነበረም። ብዙ አእላፍ ወጣት በኢሕአፓ መፈክር ሥር ሕይወቱን ከፍሏል። ያንን እንደ ታሪክ እንለፈው። በ TPLF ሥር መሰባሰብ ለሌላው ጠባብነት ነበር። ያም ታሪክ ሆነ። TPLF ዛሬ የ EPRDF አካል ነውና። ይህም ሊሆን የቻለው EPDM በመኖሩ OPDO በመፈጠሩ መሆኑን እንቀበል። ስለሆነም ከዘር ባሻገር በፍትሕ፣ በእኩልነት፣ በዴሞክራሲ ነጥቦች ላይ እንወያይ።

ለዚህ የሚጠቅመን ምንድነው? ስንል ውይይታችን የአማራና የትግራይ ከመሆን ይለፍና ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ብሩህ ተስፋ መወያየት ይሁን። አማራ ሆነን ሁለት ሚሊዮን አማራ ጠፋ ሲባል ፍለጋ እንዳልሄድን ሁሉ በትላንትናው ላይ መቆራሮሱን ትተን ለወደፊት እንዴት አብረን እንሥራ ብለን እንነሳ። ሁሉን አቀፍ ዲሞክራሲን በኢትዮጵያ ላይ ምን ብናደርግ እናጎለብታለን ብለን እንወያይ? ሃሳብ እንለዋወጥ እንጂ የተሰራውን ወጥ ያጎረናው ማነው በሚል ላይ ጊዜ አናጥፋ። ሁላችንም እንዳያር ድስቱን ማማሰሉ ላይ ችላ ባንል ኖር ዛሬ እዚህ ላይ ባልደረስን ነበር ብለን እንስማማ። የኦሮሞ ሕዝብ፣ የአማራው ሕዝብ፣ የወላይታ፣ የሲዳማ፣ የሱማሌ ሕዝብ እንደ ትግራይ ሕዝብ ችግሩን በራሱ መፍታት መቻሉን እንቀበል። ያንን ካደረግን ትልቁ ችግራችን ተፈታ ማለት ነው ብዬ አምናለሁ።

ማ ታጋይ ነበር？ ማ ምን ሰራ？ ምን አለ？በሚለው ላይ ጊዜ ከማባከን ይልቅ የተጋፈጥነው ችግር ምንድነው？ መፍታትስ እንዴት እንችላለን？ ብለን በተጋረጠው የወቅቱ ችግር ላይ ሃገራዊ ስምምነት ለመፍጠር እንጣር። በሃሳብ ያለማስማማት ደግሞ ለመስማማት መንገድ ከፋች ነው። ፈረንጆች ሲተርቱ "የመፋታት ቀንደኛው ምክንያት መጋባት ነው"The number one cause of divorce is marriage ይላሉ።

ዛሬ ዓለም እየጠበበች ባለችበት ሁኔታና ትንሽ መንደር በሆነችበት ወቅት የለም መራራቁ ይሻለናል ወደድሮው እንመለስ ብለን ብንነታረክ ከጥል ውጭ ፍቅር እናነግሳለን ማለት አይሆንም። ይህንን ገፍትረን ማከረሩን ከወደድነው ደግሞ "ልቅሶውና ጩኸቱ ከፍየሏ በላይ ሊሆን ነው" መናገር አመል የሆነብን ካለን ደግሞ ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትምና ዝም እንበልና እስቲ ማዳመጥን እንማር።

መስከኑን ያድለን

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር